# በDPS ውስጥ በሙስሊም ወላጆች በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

DPS ሕገወጥ ከሆኑ አድሎ እና ወከባ ነፃ የሆነ የትምህርት አካባቢ/ድባብ ለማቅረብ ቁርጠኛ ነው።

## አንድ የምግብ ዓይነት የአሳማ ተዋጽዖ ሲኖረው ልጄ ይነገረዋል/ታል?

የምግብ እና ሥነ-ምግብ አገልግሎት ክፍል አንድ የምግብ ዓይነት የአሳማ ተዋጽዖ ያለው ሲሆን የሚለጠፍ የአሳማ ምስል ተለጣፊ በቅርቡ ሥራ ላይ አውሏል። በአጠቃላይ፣ የDPS ቁርሶች እና ምሳዎች የአሳማ ሥጋ የሚኖራቸው በጣም አልፎ አልፎ ነው። ጥያቄዎችዎን ወይም ሀሳቦችዎን ከት/ቤትዎ የወጥቤት ኃላፊ ጋር ሊነጋገሩባቸው ይችላሉ።

## ልጄ በሙስሊም በዓላት ጊዜ ከት/ቤት እንዲቀር/እንድትቀር DPS ይፈቅዳል?

አዎ። የDPS ትምህርት ገበታ ላይ መገኘት (አቴንዳንስ) ደንብ JHB-R ሐይማኖታዊ በዓላትን ከት/ቤት ለመቅረት ተቀባይነት ያለው ምክንያት አድርጎ አካትቷል። በዓሉ እየቀረበ መሆኑን እና በዚያ ዕለት ልጅዎ ከት/ቤት እንደሚቀር እንዲያውቁ ይህንኑ ለት/ቤትዎ ቀደም ብለው ይግለጹ።

## ልጄ በት/ቤት ውስጥ እንዲጸልይ/እንድትጸልይ ይፈቀድለታል/ላታል?

አዎ። DPS ተማሪዎችን ሐይማኖታዊ ማንነታቸውን መሠረት አድርጎ መድሎ አይፈጽምም። እናም ተግባራቸው ከት/ቤት እንቅስቃሴዎች/አካባቢ ጋር የማይጋጭ እስከሆነ ድረስ ተማሪዎች በት/ቤት ውስጥ እንዲጸልዩ እና ሐይማኖታቸውን እንዲከተሉ ይፈቀድላቸዋል። ሐይማኖታዊ ፍላጎቶቻቸው ሌሎች የት/ቤት ተግባራትን/እንቅስቃሴዎችን በማያውኩ መልኩ መካሄዳቸውን ለማረጋገጥ ቤተሰቦች ከት/ቤት አመራሮች ጋር እንዲነጋገሩ እናበረታታለን።

## ልጄ ሙስሊም በመሆኑ/ኗ ወከባ ከደረሰበት/ባት ምን ማድረግ እችላለሁ?

ተማሪው ወይም አሳዳጊው ጉዳዩን ለተማሪ ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት (ለተማሪ እኩልነት/ፍትሃዊነት እና ዕድሎች ጽ/ቤት) በቃል ወይም ቅጽ AC-E2ን በመጠቀም በጽሑፍ ወዲያውኑ እንዲያሳውቁ ይበረታታሉ። "የመድሎ/የጥቃት ቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ" ከስተቱ ለልጅዎ ሰላማዊ ወይም ምቹ ያልሆነ አካባቢን የሚፈጥር ከመሰልዎ ጉዳዩን ለት/ቤት አስተዳደር ያሳውቁ። ልጅዎ ስሜቶቹን/ቿን እንዲገልጽልዎ/እንድትገልጽልዎ ያነጋግሩት/ሯት። ከዚያም በውስጡ/ጧ ያሉ የፍራቻ ወይም የመጨነቅ ስሜቶች ካሉ እንዲረጋጋ/እንድትረጋጋ ያግዙት/ዟት። በተጨማሪም ተማሪዎች በSafe2Tell አማካኝነት፡- 1-877-542-7233 (Safe2Tell.org) ሪፖርት ማድረግ ወይም በቀጥታ መስመር ቁጥር፡-720-423-3054 ለቤተሰብ እና የማኅበረሰብ ተሳትፎ ጽ/ቤት መደወል ይችላሉ።

## የDPS መምህራን የዳበረ የባሕሎች መረዳት እንዲኖራቸው ስልጠና ይሰጣቸዋል?

አዎ። ሁሉም አዳዲስ የDPS መምህራን የ1.5 ሰዓት ስልጠና የማዳላት ዝንባሌ /bias/ ላይ እና የ1.5 ሰዓት ስልጠና ባሕሎችን መረዳት ላይ እንዲወስዱ ይጠየቃሉ። ዲስትሪክቱ የ12 ሰዓቶች መሠረታዊ እና ከፍተኛ ስልጠናን የሚይዝ ለባሕል-ምላሽ ሰጭ ትምህርት ላይ የሚሰጥ የሥራ-ላይ ስልጠና (ሙያዊ ልማትን) ፣ DPS Aspire የሚባል የሁለት ቀን ስልጠና ለመምህራን መሪዎች እና ሥራ አስኪያጆች፣ መሠረታዊ እና ከፍተኛ የሆነ የማዳላት ዝንባሌ /bias/ ላይ ለሁሉም ሠራተኛ የሚሰጡ ስልጠናዎችን ጨምሮ በርካታ አማራጭ ፕሮግራምች አሉት።

## DPS አረበኛን እንደ አማራጭ ቋንቋ አድርጎ ይሰጣል?

በአሁኑ ወቅት የደቡብ /South/ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አረብኛን መማር ለሚፈልጉ ተማሪዎች አረብኛ I ብሎ ይሰጣል። እንዲሁም የአረብኛ ቋንቋ ዳራ (ባከግራውንድ) ላላቸው ተማሪዎች የውርስ (ሄሪቴጅ) አረብኛ ብሎ ይሰጣል።

## የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አረብኛ ለሆኑ ተማሪዎች DPS ሌላ ምን ድጋፍ ይሰጣል?

ት/ቤቶች ተማሪዎችን በELA ክፍሎች ውስጥ የሚያግዝ  የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አንድ ዓይነት ቋንቋ ለሆነ ለየ15 ተማሪዎች አንድ የአፍ መፍቻ ቋንቋው እንደተማሪዎቹ ቋንቋ የሆነ ረዳት አስጠኝ ይመድባሉ። በአሁን ወቅት የአረብኛ ቋንቋ አስጠኝዎች ያሏቸው ት/ቤቶች የሚከተሉት ናቸው፡- ዴንቨር ግሪን /Denver Green/ ት/ቤት፣ ኤሊስ /Ellis/፣ ሃሚልተን /Hamilton/፣ ሆልም /Holm/፣ ማክሚን /McMeen/፣ ሜሪል /Merrill/፣ ሞንትክሌር /Montclair/፣ ፕሌስ ብሪጅ /Place Bridge/፣ ሳሙኤልስ /Samuels/፣ ደቡብ / South/፣ ጆ ሹሜከር /Joe Shoemaker/፣ ሳውዝ ሙር /Southmoor/ እና ዩኒቨርሲቲ ፓርክ።

## DPS ለወላጆች የጽሑፍ ትርጉም እና የቃል ትርጉም (ቱርጂማን) አገልግሎት ያቀርባል?

አዎ፣ እነዚህ አገልግሎቶች ለወላጆች ያለክፍያ ይሰጣሉ። የጽሑፍ ትርጉም ወይም የቃል ትርጉም (ቱርጂማን) አገልግሎት ካስፈለገዎ፣ የት/ቤትዎ አስተዳደር ጥያቄውን ለDPS ብዝሃ-ባሕል (መልቲካልቸራል) አገልግሎት ጽ/ቤት እንዲያስገባ በቂ ጊዜ በመስጠት (ከተቻለ ከሰባት ቀናት በፊት) ይጠይቁት። ለድንገተኛ ወይም ለአልታሰበ ጥያቄ፣ ሁሉም ት/ቤት የስልክ ቱርጂማን አገልግሎት መስመር አለው።